ጥር 30 ቀን 2015ዓም(January 8 th 2023)

# በአማራው ላይ ያልተፈፀመ የበደል ዓይነት የለምና ቆርጦ ይነሳ!

አማራን፣ኦርቶዶክስንና ኢትዮጵያን ለማጥፋት፣የመገንጠልን ዓላማና ግብ ይዘው የሚጓዙት ጠላቶቻችን የትግሬና የኦሮሞ ነፃ አውጭዎች ! ብአዴንን እየጋለቡ፣ የፈጠሩትን ህገ መንግሥት፣የዘር ፌደራሊዝምና ሥርዓት፣ገና ከመነሻው ነቅተን፣በህቡዕ ተደራጅተንና ታጥቀን አሽቀንጥረን ለመጣል በእምቢተኝነት ከመታገል ይልቅ፣ምን ያህል የሞራል ዝቅጠት ቢጠናወተን ነው፣እነርሱ ያቋቋሙትን ገዳያችንን ሥርዓት ተሸክመን 31ዓመት ሙሉ የምንደማው።
ቀደም ሲል የትግሬን፣ዛሬ የኦሮሞን መንግሥት፣መከላከያና ፌደራል "ይድረሥልን፣ፍትህ ይሠጠን፣ህግ ይከበር" ከማለትም አልፈን እነአቢይ፣ሽመልስና አዳነች ወዘተ የኦሮሞን የመገንጠል ዓላማ ከሠፊ መሬት ጋር ከግብ ለማድረስ ግድያውንና ማፈናቀሉን ሲያጧጡፉት እያዩን፣"አቢይ ካደን፣እየገደሉን ነው" እያልን፣ወሬውን እያወራንላቸው ከጠላት ጉያ ተሸጉጠን፣መሳቂያና መሣለቂያ ሆነን ማለቃችን ሆድ ያደማል፣ያቃጥላልም።

"ለኢትዮጵያ ብለን ነው እየተበደልን የምንችለው" እንዳንል፣ኢትዮጵያም በብሄር ብሔረሰቦች ተገፍትራና ተቦርቡራ ቀፎዋ ቀርቷል።የአሜሪካን አጥኚዎች ተብዬዎችም በ2030 ዓም ከዓለም ካርታ እንደምትጠፋ የደገሱልንን ነግረውናል።ዛሬም በአደራዳሪነት ሥም በተግባር እየሠሩት ያሉትንም አልደበቁም ።

የሚሆነውንና እየሆነ ያለውን እንመልከት! ከትናንት ወዲያ በአንድነት ቆመው የፈጁን፣ትናንት ተጣልተውም የገደሉን፣ዛሬ በአሜሪካ አሥታራቂነትና ሀሳብ ሠጭነት በአንድነት ሆነው ወልቃይትና ራያን ወደትግሬ ለመመለስ ይሠራሉ።ይህንን ለመቀልበስ አማራ የሆንክ ሁሉ ከኮሎኔል ደመቀ ጎን ቆመህ እሥከምትችለው ድረስ ተዋደቅ።

ትግሬ በመጀመሪያ ከእነአቢይ ጋር የሥልጣን ተጋሪ መሥላ እንድትቀርብ ከተደረገ በኋላ፣ቀሰበቀስ ራሷን የቻለች አገር እንደትሆን እና ከፈለገች በኮንፌደሬሽን ከቀሪው ኢትዮጵያ ጋር እንድትሆን ይሠራሉ።ይህ የአሜሪካ አቋም ነው። ከ1983ዓም ጀምሮ በአሜሪካ የእጅ አዙር ቅኝአገዛዝ(Neocolonialism)ሥለወደቅን፣ካልተነሳን እንጠፋለን።

ኦሮሞም ከትግሬ በኋላ ቀስ በቀስ በኮንፌደሬሽን በሚል ሠበብ በእጁ ያላሥገባቸውን አካባቢዎች ካሥገባ በኋላ ግዙፍ አገር ይዞ መገንጠሉን ያመቻቻል።ሥለዚህ ለዚህ ተግባራቸው እንቅፋት ይሆንብናል ብለው እርቃኑን ሊይሥቀሩት ያሠቡትን አማራ በጊዜ ተረዳድተው ማጥፋት ሥላለባቸው፣"መንግሥት የለንም፣" ብለን ካልተነሳን በስተቀር፣ ከእሥከዛሬው በከፋ መልኩ፣በመንግሥት ሥም ታጥቀው ሊዘምቱብን እንደሆነ እየሠማነው ነው።

ዓለም የምታጅበውና የምትወደው ጉልበት ያለውን እንጅ ደካማን አለመሆኑን ይህ በቂ ምሥክር ነው።

ለህልውናችን ላለመቆም “መንግሥቱም፣መከላከያውም ሆነ ፌደራሉ የአማራውም ነው”፣ብለን ራሳችንን ካታለልን ግን፣”ገደሉን፣አሳደዱን፣አሠሩን”እያልን መላቀሱን ትተን፣ ባርነቱን ተቀብለሎ ሞትን መጠባበቅ ነው።

ጠላቶቻችን 31ዓመት ሙሉ በድርጅትም በትጥቅም ሲገዝፉ፣የእኛ አካሄድ ትግል ሥንጀምር ወደነበርንበት እየመለሰ፣እየመላለሰ ሥለሚወስደን፣እሰከዛሬ ድረሰ ከተናጠል፣ከተበታተነ፣ ከተሳከረ እና ግራ ከተጋባ የትግል አዙሪት ውስጥ እንድንወድቅ መሆናችንን መቀበልና አዲስ የትግል መንገድ መቀዬስ አዋቂነት ነው። ሥለሆነም

(1)አማራው! እስካሁን በጠላቶቹ በአቢይና በብአዴን ሥርዓት እየተመራና ሥልጣናቸውን እያራዘመ፣ በትግሬ የመጣበትን ችግር እፈታለሁ ብሎ ማሰቡ ወዳጅን ከጠላት የመለዬት ችግር እንዳለበት ያሳያል። ሥለዚህ ከዛሬ ጀምሮ በቅድሚያ ጠላትን ከወዳጅ ለይቶ በማወቅ ጥልቅ ንቃት ኖሮት፣ ከመሣሪያ በፊት ልቡን ያሥታጥቅ።

(2)የአማራው ልብ ከታጠቀ፣ ለሥር ነቀል ለውጥ፣ቀጣዩ ሥራ የፖለቲካ ዕውቀትና ንቃት ባላቸው ሠዎች የሚመራ፣ “ዓላማና ግብ” ያነገበ፣ጠንካራና ጥራት ያለው፣መሣሪያ የታጠቀ፣ ከማንም ተፅዕኖ ነፃ በሆነ መንገድ፣በቅድሚያ በህቡዕ፣ ጉልበት ሲፈረጥም፣በገሀድ የሚታገል የአማራ ሕዝባዊ አንድነት ድርጅት ማቋቋም ነው።

(3)ቀጥሎም የአማራው ሕዝብ መሠረታዊ ጠላቶች " ህገመንግሥቱ፣የዘር ፌደራሊዝሙና ሥርዓቱ "እንደሆኑ አውቆ ለማሥወገድ መታገል።በአዴንንም፣የትግሬንና የኦሮሞ ድርጅቶችንም ከጠላት ጎራ እንመድባቸዋለን።ይህ ሲሆን ዛሬ ካለንበት የተሳከረ ትግል ወጥተን፣ለህልውናችን ዋስትና የሆነውን የትግል መንገድ ጀመርነው ማለት ነው፡

(4) “ጠላቶቻችን የከለሉልንን አንቀበልም፣ ብሔራችን አማራ ፣ አገራችንና ክልላችን ኢትዮጵያ ናት” ብለን መፅናትና ከወለጋ ጭምር በአገሪቱ ውስጥ የሚሳደደው አማራ የሚኖርበትን አካባቢ ሳይለቅ እንዲኖር መታገል።

(5) ኢትዮጵያም ጠፍታ፣እኛም የምንጠፋ እንደሆንን ከራሳችን በላይ ምሥክር የለም።የሚያጠፉንም አገር በቀል ጉዶች ከሆኑ፣እኛ ኑረን፣ኢትዮጵያም እንድትኖር ያለን አማራጭ አንድ ብቻ ነው። ይኸውም ዳተኝነትን፣ተመፃዳቂነትንና በባዶ መኩራራትን አሽቀንጥረን ጥለን፣አማራው ተከብበ ከምድረገፅ ሳይጠፋ ነፃ ማውጣት ላይ ብቻ ማተኮር ግድ ሥለሚል ”የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው”በሚል መርህ መሠረት፣የቀደምት ጠላቶችን ጊዜያዊ ወዳጅነት ማማተር ብልህነት ነው።

በመሆኑም (ሀ) የአማራው የህቡዕ ድርጅት ተቋቁሞ በኢትዮጵያ ጫካ ከመሸገ፣አመራሩን ሳይሆን፣ የአማራን የተወሰነ ተዋጊ ኃይል ብቻ ወደኤርትራ በመላክ ሥልጠናና የመፈናፈኚያ ቦታ እንዲያገኝ ማድረግ።

ለ)አማራው ኢትዮጵያን አሥከብሮ በመኖሩ ጠላቶቹ የትዬ ሌሌ ናቸው።ትናንት ትግሬው ዛሬ ኦሮሞው ሥልጣን ላይ ቢቀመጥም የጥንት ጠላቶቻችን የአማራው ጥላው ጭምር

ሥለሚአሥፈራቸው፣ዛሬም ድረስ ቢሮክራሲውን የሚዘውረው አማራው ነው" የሚል የተዛባ አመለካከት ሥላላቸው፣ከራሳችን ላይ አልወረዱም።
ወዳጅ አልባ ሆነንና መጠጊያ አጥተን ተከብበን ከምናልቅ ወዳጅ ማፈላለግ የግድ ነው።

ሥለዚህ የአባይን ግድብ! ቀደም ሲል ትህነግ፣ዛሬ ኦሮሞ ሁለቱም አጥፊዎቻችን ሥለተቆጣጠሩት፣አማራው ጉልበት አግኝቶ ህልውናውን የሚያሥጠብቅበት ሁኔታ እስኪፈጠር ድረስ፣ዛሬ ላይ ግድቡ ለአማራው ፋይዳ የለውም።

ሥለዚህ በሱዳኖችም ሆነ በግብፆች ከጥንት ጀምሮ ዛሬም ድረስ፣የአባይ መሠረቱ የአማራው አካባቢ እንደሆነ ሥለሚያውቁ፣በአባይ ምክንያት ጭምር፣አማራው ገዥና ዋነኛ ጠላት ተደርጎ ሥለተሳለ፣ከእነርሱም ጋር ሠላም ለመፍጠር "ዛሬ አማራ እንደማይገዛና የአባይን ግድብም አማራው ተጠናክሮ ከመጣ እንደሚያሥቆመው በመሸንገል፣ለጊዜውም ቢሆን ከራሳችን እንዲወርዱ ማድረግና ሱዳን የወሰደችው መሬትም ጊዜውን እንዲጠብቅ፣ግን ገፍታ እንዳትሄድ፣በሚኖረን ድርጅት አማካይነት የዲፕሎማሲ ሥራ በመሥራት መውጪያ መግቢያ ለማግኘት መጣር።

ቀስ በቀስም ከእነግብፅ የመሣሪያም የሌላም ዕርዳታ የምናገኝበትን መንገድ ማመቻቸት የግድ ይለናል።
ይህ አካሄድ ነው ከመጥፋት የሚያድነን።ከፈረጠምንና የምንፈልገውን ግብ ከመታን በኋላ የአባይን ግድብ በእጃችን አድርገን ለመጠቀም ከልካይ አይኖረንም። ቁምነገሩ ጉልበትን ከብልህት ጋር ማዋሀድ ነው።ይህ ሀሳብ የማይዋጥለት ካለ፣የሚፈለገው እንደተለመደው ነገርን አራክሶ መተኛት ሳይሆን፣ መፍትሄ ሥለሆነ አማራጭ መፍትሄ ያምጣ።

ለፋኖዎች ያለኝ መልዕክት! ሥለፋኖነት በተደጋጋሚ ሥትናገሩ እንደሰማሁት "ፋኖ! ከመንግሥት ጋር ይተባበራል፣ ሥልጣን አይፈልግም፣ አገር ሠላም ሲሆን ወደየነበረበት ሙያው ይመለሳል፣ወዘተ" የሚል ነው፣እነ'ኚህ አባባሎች ተግባራዊ የሆኑት በአድዋ ጦርነትና በመሳሰሉት ለአገርና ለሕዝብ የቆመ ተቀባይነት ያለውና ሕዝብ ያመነበት፣ፋኖንም ያከበረ፣ውለታ መላሽ መንግሥት ሥለነበረ ብቻ ነው።ይህ አንዱ ገፅታው ብቻ ነው።

ሌላውን ገፅታ ግን አንድም ጊዜ ሥታነሱትና ሥትሠሩበት አይሥተዋልም።ይኸውም እንደ ብአዴን ለአገርና ለሕዝብ የማይቆምና ተቀባይነት የሌለው መንግሥት ከሆነ ግን፣ በአፄ ሱስንዮስ ላይ የተደረገውን ከተረዳችሁ፣ዛሬ በብአዴንና በኦሮሞ መንግሥታት ተብዬዎቹ እሥከምትታደኑ አትጠብቁም ነበር።

"አፄ ሱስንዮስ! ካቶሊክ ሆኛለሁና ሕዝቤም ካቶሊክ ሁን" ብለው ሲያውጁ፣ሕዝባዊ ፋኖው ከቤተ መንግሥቱ አባላት ጭምር በአንድ ተሠልፎ ፣በንጉሱና በደጋፊዎቹ ላይ የሥምንት(8) ዓመት ጦርነት አካሂዶ "ሀይማኖት ይመለስ፣ፋሲል ይንገስ"ብሎ በማወጅ፣ የአፄ ሱስንዮስን ልጅ አፄ ፋሲልን በማንገስ ድሉን በእጁ አድርጓል።የዚያን ጊዜው ፋኖ በዓይኑ ላይ ሥለመጡበት መንግሥትን አልተባበረም።ተዋግቶ መንግሥትን ከለወጠ በኋላ ሥልጣንም ተቋዳሽ ሆኗል።የዛሬዎቹ ፋኖችም ከዚህ ውጭ ሌላ የመፍትሄ መንገድ እንደሌላችሁ፣መሳደዳችሁ ምሥክር ነው።